ACPS

Alexandria City Public Schools



# የበጎ ፈቃደኞች መመሪያ

## እንኳን ደህና መጡ! እናመሰግናለን!

በአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስለሰጡ እናመሰግናለን (ACPS) ። ለትምህት ቤታችን ቀጠናና ለተማሪዎቹ በጣም ጠቃሚ የሆነ አስተዋጽኦ እያደረጉ ሲሆን የእርስዎን ጊዜ፣ ጉልበትና ሙያ እንደምናከብር እንዲያውቁልን እንፈልጋለን። እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሳካለት ስላገዙን እናመሰግናለን።



Alvin L. Crawley, Ed.D.
የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ





# ገጽ ማውጫ


በጎ ፈቃደኛ ለመሆን ........ 4

የበጎ ፈቃደኛ የጸባይ ደንብ ........ 5

የበጎ ፈቃደኞች ማወቅ ያለባቸው መመሪያዎችና አካሄዶች ........ 6

ለበጎ ፈቃደኞች ጠቃሚ ምክሮች ........ 8

ከተለያዩ ባህሎች ከመጡ ተማሪዎች ጋር መስራት። ........ 8

የበጎ ፈቃደኞች መረጃ/አካሄድ መከታተያ ........ 9

የበጎ ፈቃደኛ ሰራተኛ ማውጫ ........ 9

# በጎ ፈቃደኛ ማን ነው?

በጎ ፈቃደኛ ማለት ደመወዝ የማይከፈለው በትምህርት ቤቱ ክፍል የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንዲሰጥ በኤሲፒኤስ ፈቃድ ያገኘ፡፡ ይህም ማንኛውም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ከኤሲፒኤስ ተማሪዎች ጋር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ግንኙነት ያለው፡፡ ለተጨማሪ መረጃ ኤሲፒኤስ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ የትምህርት ቤቱን የበጎ ፈቃደኞች በተመለከተ ይህንን ይመልከቱ
http://www.acps.k12.va.us/board/manual/iicb.pdf.

# በጎ ፈቃደኛ ለመሆን

1. በኤሲፒኤስ ትምህርት ክፍል/ትምህርት ቤት ውስጥ የበጎ ፈቃኛ አገልግሎት ለመስጠት በመጀመርያ ኢንተርኔት ላይ ያለውን መመዝገቢያ ፎርም መሙላትና ማስረከብ አለብዎት https://alexandria.keepntrack.com/apply የወንጀልና የጾታ ጥቃት ማድረስዎን የጀርባ ጥናት ይደረጋል፡፡ ብቁ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች ወላጆችን፣ አሳዳጊዎችን ጨምሮ የጾታ ጥቃት ማድረሳቸው የተመዘገቡ የኤሲፒኤስ የጾታ ጥቃት ማሳወቂያ ምዝገባ ፖሊሲን ማነጋገር ይኖርባቸዋል፡፡ (ፋይል ኬኤን) እና የኤሲፒኤስ የተመዘገቡ የጾታ ጥቃት ያደረሱ በትመህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ፖሊሲ (ፋይል  ኬኤንኤ).
2. ማመልከቻውን በተሟላ ሁኔታ ካስገቡ በኋላ ባሉት አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ የፈቃደኝነት ኢሜል ይደርስዎታል፡፡ ይህም የፈቃድ ኢሜል ኤሲፒኤስን ቤተሰብ እና ህብረተሰብ ጋር የሚኖር ግንኙነት ማዕከል እንዲገናኙ እና አስፈላጊውን የማረጋገጫ መስፈርት ኣካሄድ እንዲጨርሱ ይመራዎታል፡፡
3. 3. ተቀባይነት ያለው የመንጃ ፈቃድ ወይም ሌላ በመንግስት በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ ለማረጋገጫነት ለመጠቀም በቀጠሮ ቀን ይዘው መቅረብ ይኖርብዎታል፡፡ ኤሲፒኤስ የበጎ አገልግሎት ጥያቄን ያለ የህብረተሰብ ደህንነት ቁጥር እና በተባበሩት የአሜሪካ መንግስት በተሰጠ መታወቂያ ውጪ ለመመልከት አይችልም ፡
4. 4. አንዴ ከተረጋገጠ በኋላ የመታወቂያ ቁጥር ያለውና የባር ኮድ ያለው የኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኛ ባጅ እና የፎብ ቁልፍ ይሰራልዎታል ፡፡
5. 5. ለመግባትና ለመውጣት በየትምህርት ቤቶች በሚገኙት ኪዮስኮች በመጠቀም ሁሌም ቢሆን የፎብ ቁልፍዎትን ይጠቀሙ፡፡
6. 6. በትምህርት ቅጥር ግቢ ውስጥ እስካሉ ድረስ ሁሌም ቢሆን የተዘጋጀልዎትን የበጎ ፈቃደኛ ባጅ በሚታይ ቦታ ላይ ማንጠልጠልዎን አይዘንጉ፡፡
7. 7. የበጎ ፈቃደኞች የመመዘኛ ሂደት በጎ ፈቃደኞችን ፈቃድ የሚሰጣቸው ለአንድ ዓመት ያህል ጊዜ ነው፡፡
8. 8. በጎ ፈቃደኞች ፈቃዳቸው ሊያልቅ አንድ ወር ሲቀረው ማስታወሺያ ይላከላቸዋል እናም እንደአዲስ የጀርባ ጥናት እንዲካሄድ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል፡፡ በጎ ፈቃደኞች በዚህ የበጎ ገቃኛነት አገልግሎት ለመቀጠል የሚፈልጉ ከሆነ በጽሁፍ መልስ መስጠት አለባቸው፡፡ እንደ አዲስ የጀርባ ጥናት ይካሄዳል፡፡ ፈቃድ ከተሰጠ የመጀመሪያው የበጎ ፈቃደኛነት ባጅ ለአንድ ዓመት ይታደሳል፡፡ በጎ ፈቃደኛውም በኢሜል እንዲያውቅ ይደረጋል

# ኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኛ የሚጠበቁ እና የስነ-ምግባርደንብ

ይህ የስነ-ምግባር ደንብ ከሁሉም የአሌክሳንደሪያ የህዝብ ት/ቤት የኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኞች የሚጠበቀውን የገልጻል እና የበጎ ፈቃደኞችን እና የሚያገለግሏቸውን ተማሪዎች ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲያግዝ የተዘጋጀ ነው።

**እንደ የኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኞች አባልነቴ የሚጠበቅብኝ እና በዚህ የስነ-ምግባር ደንብ መመሪያ መሰረት እገዛለሁ**

1. ወዲያውኑ እንደደረስኩ በዋናው ቢሮ ወይም ለዚህ በተቀመጡት ቦታዎች መግቢያ ምልክት አደርጋለሁ፡in እንዲሁም በመውጫ ሰዓት የበጎ ፈቃደኝነት ስራዎቼን እንደጨረስኩ ደግሞ የመውጫ ምልክት በማድረግ እወጣለሁ::
2. በኤሲፒኤስ ጋር የበጎ ፈቃኛነት ስራ በምሰራበት ጊዜ የበጎ ፈቃደኛ መታወቂያ ባጄን ሁሌም ቢሆን አደርጋለሁ::
3. ባለማርገድ እና ባለመቅረት የቀን ውሎዬ እንዲመዘገብ አደርጋለሁ:: መቅረት ቢኖርብኝ ወይም ማርፈድ ቢኖርብኝ ወዲያውኑ የበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪውን ወይም እንድናገኘው የተደረገውን ሰው ኣሳውቃለሁ::
4. ጥሩና ተከታታይ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረኝ አደርጋለሁ ከበጎ ፈቃድ አስተባባሪው ጋር እና ከስራ ፡ ባልደረቦች ጋር::
5. መልካም የሆነ አስተሳሰብ እንዲኖረኝ አደርጋለሁ:: ማንኛውም አሳሳቢ ነገሮችን ወይም ቅሬታዎችን ወደ ተገቢው የት/ቤቱ ሰራተኛ ወይም አስተዳዳሪ እመራለሁ።
6. የተማሪዎቼን ሚስጥር በማንኛውም ጊዜ እጠብቃለሁ:: ስለ ተማሪዎቹ ከማንኛውም ሰው ጋር አላወራም ከኤሲፒኤስ አስተማሪዎች፣ አማካሪዎች፣ እና/ወይም የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ስለ ወሬው ህጋዊ የሆነ የትምህርታዊ ፍላጎት ያላቸው ካልሆኑ በስተቀር::
7. ስለተማሪዎቹ የሚኖረኝ ማንገውም የጤንነት እና የደህንነት ጥያቄዎችን ከአስተማዎችና ወይም የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጋር እወያያለሁ::
8. ስለ ልጆች ጥቃት ለጁ መጥቶ ከነገረኝ ወይም የጥቃት ሁኔታ ከታዘብኩ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር አሳወቃለሁ:: ሰራተኛ ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት እና መከታተል እንዳለበት እረዳለሁ::
9. ሁሉንም የተጠቀሱትን መመሪያዎች እና አካሄዶች በትምህርት ቤቱ/በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሁሉ እከተላለሁ (ይህም ማለት የእሳት አደጋ ጊዜ ልምምድ፣ የጉዳት ሪፖርት፣ የምሳ ፈቃድ፣ የማይመቹ የአየር ንብረት ሁኔታዎች ጊዜ የሚደረጉ አካሄዶች ወዘተ...)
10. የአዋቂ የመጸዳጃ ቤቶችን ብቻ እጠቀማለሁ::
11. በተቻለኝ ጊዜ ሁሉ ብቻየን በተናጠል ከአንድ ተማሪ ጋር አልሆንም።
12. የአካላዊ ቅጣት አልጠቀምም። አስቸጋሪ ጸባይ ካላቸው ተማሪዎች ሲሆኑ አስተማሪውን ወይም የት/ቤቱን ሰራተኛ እንዲረዳኝ እጠይቃለሁ
13. ተማሪዎችን ከትምህርት ሰዓት ውጪ ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊ ፈቃድ ውጪ አላገኛቸውም::
14. ስለ ተማሪዎች የሚገልጽ ማንኛውንም አየነት ፎቶግራፍ ወይም የግል መረጃ ወይም ስለ ራስ ወይም ስለ ሌሎች አልገልጽም::
15. ከኤሲፒኤስ ኮምፒውተርን በሃላፊነት የመጠቀም ፖሊሲ አንብቤ በዛው መሰረት እገዛለሁ (ፋይል: አይአይቢኢኤ/ጂኤቢ).
16. በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በምሆንበት ሰዓት በናቸውም አደንዛዥ እፅ ወይም አለኮል መጠጥ ወይም ሲጋራ ተፅዕኖ ስር አልሆንም::
17. በማንኛውም ወንጀል ወይም የጾታ፣ የአደንዛዥ እፅ ወይም ከአደገኛ መሳሪያ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ወንጀል ፡ወይም ተመሳሳይ ወንጀል ከታሰርኩ የትምህርት ቤቱን አስተዳደር ወይም ተገቢውን የትምህርት ክፍል ሃላፊ አሳውቃልሁ::
18. የተማሪዎችን የራሳቸውን አስተሳሰብና የአመጣጥ ሁኔታ አከብራለሁ::
19. ሁሌም ቢሆን ለማገኘው እያንዳንዱ ተማሪ የሚኖረውን የግል እና የትምህርታዊ ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር ብቻ እሰራለሁ::
20. የኤሲፒኤስ የጾታዊ ጥቃት ፖሊሲ አንብቤ በዛው መሰረት እገዛለሁ (ፋይል ጆቢኤ/ጂኤፍኤችኤ)::

**የኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኛ የስነ-ምግባር ደንብን በማንኛውም ጊዜ ለመከተል አልያም የበጎ ገቃደኛነቱን ወዲያውኑ ለማቋረጥ እስማማለሁ::**

# የበጎ ፈቃደኞች ማወቅ ያለባቸው መመሪያዎችና አካሄዶች

## ጾታዊ ትንኮሳ

ኤሲፒኤስ ከጾታ ትንኮሳና በዘር፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት፣ በሀይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታዊ ማንነት፣ ጾታን በመግለፅ ወይም በጾታ ፍላጎት ሁኔታ ላይ ከተመሰረተ ትንኮሳ ነፃ የሆነ የትምህርት/የስራ ሁኔታ እንዲፈጠር ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፡፡ ስለዚህም የአሌክሳንድሪያ የከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ በማንኛውም ተማሪ ወይም የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ወይም ትምህርት ቤቱ የሚያደርጋቸው የድጋፍ እንቅስቃሴዎች ላይ የጾታ ትንኮሳንና በዘር፣ በብሔር፣ በአካለ ስንኩልነት፣ በሀይማኖት፣ በጾታ፣ በጾታዊ ማንነት፣ ጾታን በመግለፅ ወይም በጾታ ፍላጎት ሁኔታ ላይ ከተመሰረተ የሚደረግ ትንኮሳን በጥብቅ የከለክላል፡፡ ለበለጠ መረጃ ይህንን ይመልከቱ http://www.acps.k12.va.us/board/manual/gba.pdf.

## ሀላፊነት የተሞላበት የኮምፒውተር አጠቃቀም

ኤሲፒኤስ እና ሰራተኞቹ ቴክኖሎጂን በቀጣይነት፣ በኃላፊነት እና በአዋጪነት ለመማር ማስተማር፣ ለግንኙነት እና ለውጤታማነት ለመጠቀም ይጥራሉ፡፡ ኮምፒውተር በሚያገኙበት ጊዜም ከሚሰጣቸው የጊዜ አጠቃቀም ወይም የሚጠቀሙበት አይነት ወይም ይዘት ያለአግባብ መሆን የለበትም፡፡ የኤሲፒኤስ ኮምፒውተርን የሚጠቀም ማንኛውም ግለሰብ በዚህ አጠቃቀም ዙሪያ የግል ምስጢሩ እንዲጠበቅለት አይጠብቅም፡፡ ለበለጠ መረጃ ይህንን ይመልከቱ http://www.acps.k12.va.us/board/manual/gab.pdf

## የሃላፊነት ኢንሹራንስ

በጎ ፈቃደኞች በኤሲፒኤስ የሃላፊነት ኢንሹራንስ እቅድ ውስጥ የታቀፉ ናቸው በጎ ፈቃደኛው“በስራ ላይ በተያያዘ” ድርጊት በሚደርስበት/ባት ጉዳት ላይ ለኢንሹራንስ ጥቅማጥቅም ብቁ ሊሆን/ልትሆን ትችላለች፡፡“ኢንዱስተሪያል ጉዳት”፤ የበጎ ፈቃደኛ ስራን በመስራት ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ወይም ህመም ሲከሰት ከታች የተጠቀሱትን መከተል ያስፈልጋል፤

- ምንም እንኳን የደረሰብዎት ጉዳት እጅግ በጣም ትንሽ ቢሆንም የደረሰብዎትን ጉዳት ለትምህርት ቤቱ ወይም ክፍል አስተዳደር ቢሮ ወዲያውኑ መሳወቅ፡፡
- ህክምና የሚያስፈልገው ነገር ከሆነ፣ ትምህርት ቤቱ ወይም የክፍል አስተዳደሩ የጤና፣ የደህንነት፣ እና የሃላፊነት አስተዳደር ተቋማትን ማገናኘት አለበት 7036198295.

ኤሲፒኤስ አስቀድሞወደ ህክምና ተቋም ወይም ወደ ሀኪምዎ እንዲሄዱ ሊፈቅድልዎት ይገባል፡፡

## የበጎ ፈቃደኞች ከ ተማሪዎችና ከቤተሰቦቻቸው ጋ የሚኖራቸው ግንኙነት

የኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃደኞች ፕሮግራም ስኬት የሚለካው የኤሲፒኤስ በጎ ፈቃደኞች፣ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች እና በአጠቃላይ ህብረተሰቡ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ነው፡፡ በጎ ፈቃደኛም ሆኑ ተቀጣሪ አባል፣ እርስዎ የኤሲፒኤስ አምባሳደር ነዎት፡፡

## የአለባበስ ስነ ስርዓት

በጎ ፈቃደኞች በህብረተሰቡ እና በስራ ቦታ አለባበስ መለኪያ መሰረት ተቀባይነት ያለውን ልብስ መልበስ አለባቸው፡፡ በሚኖርዎት የአለባበስ ስነ ስርዓት ስለተቀባይነቱ እርግጠኛ መሆን ካልቻሉ እባክዎ የበጎ ፈቃደኞችን አስተባባሪ ወይም የትምህርት ቤቱ/የክፍል አስተዳደሩን ያነጋግሩ፡፡

## እህትማማች/ወንድማማች ተማሪዎች

እንደ አጠቃላይ ህግ ወላጆች ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ወደ ትምህርት ቤት በሚመጡበት ወቅት የተማሪዎች ታናሽ እህቶች/ወንድሞች አብረው መምጣት የለባቸውም። እድሜያቸው ለትምህርት ቤት ያልደረሱናና ትንንሽ እህቶች/ወንድሞች ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችንና በጎ ፈቃደኛ ወላጆችን ሊያስቸግሩ ይችላሉ። በተጨማሪም ታናናሽ እህቶች/ወንድሞች በትምህርት ቤት ውስጥ ለራሳቸው ደህንነት ሲባል በጥንቃቄ ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል። በበጎ ፈቃደኞች ጥቅም ላይ ከሚውሉት መሳሪያዎች ውስጥ አንዳንዶቹ እድሜያቸው ለትምህርት ላልደረሱ ህጻናት ደህንነት ስጋት ስለሆኑ ህጻናቱ የማይደርሱበት ቦታ መቀመጥ አለባቸው (ማሽኒያ ማሽኖች፣ የወረቀት መቁጠሪያዎች፣ መቀሶች፣ ስቴፕለር ምቻዎች፣ የኮፒ ማሽኖች፣ ወዘተ)።

## የቢሮ ማሽኖች

ሰራተኞች በክፍል ውስጥ የመማሪያ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚያግዙ በጎ ፈቃደኞችን ያደንቃሉ። በጎ ፈቃደኞች ሁሉንም የቢሮ መሳሪያዎች አጠቃቀም በተመለከተ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል። በተጨማሪም በጎ ፈቃደኞች መምህራን ወይም ሰራተኞች መሳሪያዎቹን ለአስቸኳይ ስራ በሚፈልጉበት ወቅት ዞር ብለው መምህራኑ ወይም ሰራተኞቹ ማሽኖቹን እንዲጠቀሙበት ቢፈቅዱላቸው መልካም ነው። የኤሲፒኤስ መሳሪያዎች ለትምህርት/ለትምህርት ቤት አገልግሎት ብቻ የሚውሉ ሲሆን ለግል አገልግሎት አይውሉም።

## መኪና ማቆሚያ ቦታ

በትምህርት ቤት አቅራቢያ ወይም በትምህርት ቤት የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ሲያሽከረክሩ ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብዎ ሲሆን በማንኛውም ጊዜ ተማሪዎች ወይም ሌሎችን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልጋል። መኪናዎን የት ማቆም እንዳለብዎ መረጃ ለማግኘት ከትምህርት ቤቱ ቢሮ ይጠይቁ።

## ስርቆት

ማንኛውም በኤሲፒኤስ የተገዛ ወይም የቀረበ ንብረት ያለ በጎ ፈቃደኞች አስተባባሪው ወይም ትምህርት ቤቱ/ ትምህርት ክፍሉ በግልጽ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ከትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ መውጣት የለባቸውም። በጎ ፈቃደኞች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ወይም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ንብረት ወደ ትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ ይዘው መምጣት የለባቸውም።

## በፈቃድ መልቀቅ/መሰናበት

በማንኛውም ምክንያት ለኤሲፒኤስ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠትን ለማቆም ከወሰኑ እባክዎ ለበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪው ወይም አብረዎት ለሚሰሩት በቀጥታ ያስታውቁ፡፡ ኤሲፒኤስ ከማንኛውም ሰው ጋር ያለውን የበጎ ፈቃደኛ ግንኙነት የማቋረጥ ሙሉ መብት አለው፡፡



# ለበጎ ፈቃደኞች ጠቃሚ ምክሮች

1. ከተማሪዎች ጋር ሲሰሩ ትግስት ይኑርዎት። በደንብ እስኪላመዱት ድረስ ለራስዎ ጊዜ ይስጡት።
2. ስሞች በጣም ጠቃሚ ናቸው። የተማሪውን ስም ተማሪው በሚፈልገው መንገድ እንደጠሩት እርግጠኛ ይሁኑ። በትክክል እንደጻፉት እርግጠኛ ይሁኑ። ተማሪዎች ስምዎን እንደሚያውቁትና በትክክል እንደሚጠሩዎት እርግጠኛ ይሁኑ።
3. ሰዎችን በአክብሮትና በትህትና ያስተናግዱና ይህንኑ ከእነሱ ይጠብቁ።
4. ተማሪዎቹ የሚናገሩትን በአግባቡ በማዳመጥና እንደሚያስቡላቸው በቃላትና በተግባር በማስረዳት በእያንዳንዱ ተማሪ ላይ ፍላጎት ያሳዩ።
5. የተማሪውን ስኬት ያበረታቱና ይደግፉ። በእውነተኝነትና በተደጋጋሚ በማሞገስ የራስመተማመናቸውን ይገንቡ። ትኩረት መስጠትና ጥረት ልክ እንደ ብቃት እንደሚቆጠሩ ያስታውሱ። አወንታዊ ነገሮች ላይ በመገንባት አሉታዊ ነገሮችን ይቀንሱ።
6. በተማሪዎች መካከል፣ በመምህራን መካከልና በትምህርት ቤቶች መካከል ንጽጽር ማድረግ ያቁሙ።
7. ሁልጊዜም ፍትሃዊና ተመሳሳይ እርምጃን የሚወስድ መሆንን ያስታውሱ።
8. ተማዎች ይሳሳታሉ። መሳሳት የመማር አንዱ አካል እንደሆነ ያሳውቋቸው። እርስዎም ስህተት መስራትን አይፍሩ።
9. በአቀራረብዎና ለሌሎች ባለዎት አመለካከት እምነት የሚጣልብዎ ይሁኑ። “እውነተኛ”ሲሆኑ ተማዎች እምነትና ክብር ይሰጡዎታል።
10. ግዴታ መቅረት ካብዎ ለትምህርት ቤቱ ደውለው ያሳውቁ። ተማዎቹ መምጣት ባለመቻልዎ ይበሳጫሉ ነገር ግን አስበው በመደወልዎ ደስተኛ ይሆናሉ።

# ከተለያዩ ባህሎች ከመጡ ተማሪዎች ጋር መስራት።

በኤሲፒኤስ ባሉት የተለያዩ ብሄሮች ምክንያት ልጆቹ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሲሆን የተለያዩ እምነቶችና ልማዶች አሏቸው። የባህል ልዩነቶች የተማሪው ቀደምት እውቀት፣ የመማሪያ ስልት፣ ባህሪይና ማህበራዊ ክህሎቶች ላይ ተጽእኖ ሊያመጡ ይችላሉ። በተለይም የሚከተሉትን በተመለከተ የባህል ልዩነቶች ሊያጋጥሙዎ ይችላሉ፦

- የተለያዩ የትምህርት ስልቶች
- አይን ለአይን መተያየት
- ስለ ጊዜ ያለ ግንዛቤ
- ስነምግባር አጠባበቅ
- የተማሪ መነሳሳት
- የግል ተብለው የሚወሰዱ ክፍተቶችና ተገቢ የሆነ አካላዊ ንክኪ

የተማሪዎቹን ባህል መረዳትና የትምህርት ቤቱን ባህል እንዲረዱት ማገዝ እነሱን የማስተማር ብቃትዎን ያሳድገዋል።

# የበጎ ፈቃደኞች መረጃ/አካሄድ መከታተያ

ለመጀመሪያ ጊዜ የበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪዎን፣ መምህርዎን እና/ወይም ተቆጣጣሪዎን ሲያገኙ የሚከተሉትን በተመለከተ ለመወያየት ያቅዱ።

- ለበጎ ፈቃደኞች ክፍት የሆኑ መርሃ ግብር የተያዘላቸው ቀናትና ጊዜዎች።
- በበጎ ፈቃደኛውና በበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪ/የተመደበ ሰራተኛ መካከል ለሚኖረው ቀጣይነት ያለው ግንኙነት መንገዶች (መደበኛ ኮንፍረንሶች፣ የስልክ ውይይቶች፣ ማስታወሻዎች፣ መደበኛ ያልሆኑ ስብሰባዎች)።
- መምህሩ/ተቆጣጣሪው በማይኖርበት ጊዜ የሚኖሩት አማራጭ እቅዶች።
- የትምህርት ቤት/የትምህርት ክፍል ፖሊሲዎችን፣ አሰራሮችንና ደንቦችን (እንደ የበጎ ፈቃደኞች አስተዳደር ስርዓት፣ የድንገተኛ ጊዜ አሰራሮች፣ በጎ ፈቃኞች የግል ንብረቶቻቸውን የት እንደሚተዉ፣ ወዘተ)።
- የበጎ ፈቃደኞችን መቅረት/መዘግየት በተመለከተ ለትምህርት ቤቱ/ትምህርት ክፍሉ ማሳወቂያ መንገድ።

# የበጎ ፈቃደኛ ሰራተኛ ማውጫ

በእያንዳንዱ የኤሲፒኤስ ትምህርት ቤት/ትምህርት ክፍል ያለው የበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪ ወይም የተመደበው ሰራተኛ ምደባዎን በተመለከተ ስለሚኖርዎት ጥያቄዎች፣ ስጋቶች ወይም ችግሮች ሊያግዙዎ ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| የተመደቡበት ትምህርት ቤት | |
| የትምህርት ቤቱ ስልክ | |
| የትምህርት ቤቱ አድራሻ | |
| ሃላፊ (ፕሪንሲፓል) | |
| የትምህርት ቤቱ ጸሃፊ | |
| የበጎ ፈቃደኛ አስተባባሪ/የሚያገኙት ሰው | |
| መምህር(ራን) | |
| ሌላ የሚያገኙት ሰው (ሰዎች) | |

አንድ ተማሪን በተመለከተ ለተፈጠረ ችግር መፍትሄ ማግኘት ካልቻሉ የትምህርት ቤቱን ሃላፊ (ፕንሲፓል) ወይም የቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ ማዕከሉን (Family and Community Engagement Center) ማግኘት ይችላሉ:

**የቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ ማዕከል (Family and Community Engagement (FACE) Center)**
**(703) 824-6865**
**www.acps.k12.va.us/getinvolved/volunteer**

Family and Community Engagement Center (FACE)

Engaged Families, Successful Students

**(703) 824-6865**

**www.acps.k12.va.us/getinvolved/volunteer**